# ኢትዮጵያዊ መልኩ

*በመጽሐፍ ቅዱስ ወስጥ ስማቸው ተደጋግሞ ከተነሱት አገሮች መካከል ኢትዮጲያ አገራችን አንዷ ነች። ከተነሱትም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችና ንባቦች በአብዛኛው የህዝቦቿ በዚህች ምድር ላይ መመላለስ የአምላካቸው መልካም ፍቃድና ቀናዊ አመለካከትን የሚያንፀባርቁ ናቸው። የተፃፈላትም ቀና ቀናውን ሞገስ ሞገሱን ነው። ". . . ለኔ እንደ ኢትዮጵያውያን ሊጆች አይደላችሁምን ?" ትንቢተ አሞጽ 9:7 እስከሚል ድረስ።*
*ይሄ እንዲሁ የመጣ አይደለም ቀደምት አባቶቻችን ለእግዚአብሄር ታዛዥና መንገዳቸው አምላካዊ በመሆናቸው ነው። ያላቸው ቀናነት ለእርሱ ለአምላካችን ፅኑ ፍቅርና መታዘዝ ከአህዛብ መካከል ከአህርያም ተመለከታቸው። ለዚህም ይመስላል በኦሪቱ በሙሴን ጽላት ፣ በአዲሱን በግማደ መስቀል ያከበራቸው።*

*የቀደሙ መሪዎችም ሃይማኖተኞች በመሆናቸው ፍርዳቸውም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለበት እንደ ነበረ ታሪካቸው ይመሰክራል። ከንግስናቸው በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያናትን ሲያሳንፁ ፣ ገዳማትን ሲያሰሩ ኖረው አልፈዋል። የንግስና ዘውዳቸውን አውልቀው ስልጣንንና አለምን ንቀውና ቢቃኝ ብለው በምንኩስና ጳንጠሊዮ ገዳም የገቡትን አፄ ካሌብን ማንሳቱ ከምሳሌ በላይ ነው።*

*አክሱማውያን ፣ ላስታውያን ፣ የጎንደር ፣ የሸዋና የሌላው ክፍል ነገስታት መንፈሳዊ አካሄዳቸው ለህዝባቸውና ለአገራቸው ሰላም ፣ ብልፅግናና ደህንነት ያደረጉት አስተዋፅዖ አሻራው ዘመን ተሻግሮ አሁንም ይታያል። ህዝቡን በውህደት ስሜት አስተሳስሮ አጣምሮ አልፏል። የጋራ የሆነ ጉዳይ ፈጥሮ ፣ የጋራ አገር አበጅቶ ፣ የጋራ ጠላትን በጋራ ተዋግቶ ፣ በጋራ ሸንፈት ፣ በጋራ ድል እኩል ውህደትን ፈጥሮ እዚህ ደርሷል።*

*የኢትዮጵያ ህዝብ ጉልበቱ ፣ ጥንካሬውና ድሉ ፈሪሃ እግዚአብሄነቱና የዘመናት የአብሮነት ውህደት ነው። ሃይማኖቱን ለመዋሃዱ ፣ ሃይማኖቱ ፈጣሪውን ለመቅረብ ይተጋበታል እንጂ ለመለያያው አሰቦት አያውቅም። ከገጠር እስከ ከተማ ያለው ህዝብ ሳይማር የተማረ ፣ ለነገሮች ሁሉ ሚዛናዊ የሆነ ፣ ከህገ ልቦና አልፎ ፣ በህገ ሃይማኖት ፀንቶ የኖረ ፣ አሁንም ያለ ነውና ዘመንን እያሰለሰ ለመፍረሱ ፣ ለመበተኑ የተደገሰለትን የከፋት ምክንያትን ያልተቀበለው ለእዚህ ነው። የኢትዮጵያን ህዝን የኋላ ታሪኩን ስናይ ጥሩ መሪዎቹን ተከትሎ ፣ ሃይማኖቱና አባቶቹን አክብሮ የኖረ ህዝብ ነው። ጠላት መጣ ቢሉት ተዋግቶ ስጋና አጥንቱ በአንድ ጉድጓድ ቀብሮ ክብሯን መላልሶ አቁሞላታል።*

*በተቃርኖ ግን ላለፉት ሃምሳ (50) አመታት ወደ ስልጣን መጣን ያሉት መሪዎች ለዚህ ህዝብና ለዚህች አገር መካራን ፣ ስቃይን ፣ ስደትን ፣ ርሃብንና ጉስቁልናን ይዘውለት መጥተዋል። ቀናት ፣ ወራትና አመታትን አልፈው እንኳን ይህንን የሚያወርዱበትን ወርጅብኝ ሊያስቀሩለት ወደ መልካም ጎዳና ሊመልሱትና ሊመሩት አይፈልጉም ወይንም አልቻሉም ። በተለይ የአሁኖቹ ለአገርም ለወገንም ለዛሬም ይሁን ለውደፊት ለሚፈጠረው ነገር ግድ የሚላቸው አይደሉም።*

*ርሃቡን ሰደቱንና መከራውን ሊያስታግሱለት ቀርቶ ፣ የአገሪቷን ድንበር ከማስደፈር አንስቶ የመሳሪያቸው ቃታ ከህዝቡ ግንባርና ከደረት ላይ ሊያስወግዱለት አልቻሉም። ህዝብ ከመሳሪያ በላይ ጉልበት ያለው አልመስላቸው አለ። አገሪቷን ዛሬውኑ እንደልብስ ለብሰዋት ፣ እንደጫማ ተጫምተዋትና ጨርሰዋት ለነገው ትውልድ ላያስረክቧት ቆርጠው የሚደክሙ እንደሆኑ ውስጠ አዋቂዎች ይናገሩታል። ያየነውም እውነታ ይሄው ነው።ገበያ ሙሉ ህዝብ ፈጅተው አስፈጅተው ፣ ህፃናት ከነትምህርት ቤት በቦንብ*

*አውድመው ፣ ሰፈር አቃጥለው አይተናል ሰምተናል። የስልጣን ብልግናቸውን ፣ በአገር ንብረት ላይ የሚያደርሱትና እያደረሱ ያሉት ሃብት ዘረፋ መቼም ቢሆን ጠባሳው እንደማይሽር እንኳን ለምጣኔ ሃብት ባለሙያ ለተራው ሰውም ስጋቱ ድብቅ አይደለም። ሃገራዊ ምሰሶ የሆነውን የህዝቦችን አብሮ የመኖር ማገሩን ለማፍረስ በብረት መዶሻ ይቀጠቅጡታል። ኣይን ያወጣው የሩብ ምዕተ አመት የውያኔ የተንኮል ስራ ያስከተለው የመራራቅ ጥፋት ትንሽ ነው ባይባልም የፈለጉትን ያህል ባለመሆኑ አጥፊዎችን ቢያናድድም መልሶ ለመገንባት የህዝብ ፅኑ ፍላጎትን ይጠይቃል።*

*ምስጋና ለእግዚአብሔር ፣ እድሜ እና ክብር ለኢትዮጵያ ህዝብ ይሁን እንጂ የደገሱለትንማ እነርሱ ያውቁታል። ትናንት የነበረ ፍቅሩ ለዛሬ ስንቅ ባይሆነው ኖሮ በዘረኝነት ጠኔ ከፉኛ ተጎድቶ ፣ አገሩንም የከፉ ደረጃ ላይ ባደረሳት ነበር። ከዚህ ሁሉ መከራ በኋላ " የእከሌ ብሄር ደም የኔም ደሜ ነው . . ." ብሎ መባባል ከመስማት በላይ የሚስደስት ነገር የለም። ጠላቶቹ የመቃጠያ እሳታቸውን ከቅርብም ከሩቅም በግልጽ እያዩት ነው። ታዲያ ይህንን እሳት እነርሱ ስለማየታቸው እርግጠኞች አይደለንም።*

## *ኦርቶዶክሳዊነት ሃይማኖት*

*በቤተ ክርስቲያን አጠራር እኔ "ጨዋ . . ."(ምንም እማያውቅ) ከሚባሉት ጎራ እንደሆንኩኝና አባቶችን የመሞገቱ የሞራል ብቃቱ እንደሌለኝ አውቃለሁኝ። ግን በዚህ ዘመን የምናየው በኦርቶዶክስ እምነትና አስተምሮት ጉዳይ ላይ ግን ለተራ ምዕመንም ፍንትው ብሎ የወጣ የአደባባይ ምስጢር ስለሆነ ማገናዘብ እንጂ ምሁርነት የሚያስፈልገው አይደለም። "ነገር በአይን ይገባል . . ." እንዲሉ ነገር የምናየውና የምንሰማው ሁሉ ያሳዝናል ያሳስባልም።*

*የሃይማኖት ልጆቻቸው እሚያይዋቸው እማይመስላቸው የሃይማኖት አባቶችና ወንድሞች በቁጥር አንድና ሁለት ብቻ ናቸው ብለን ከምንለው በላይ ሆነዋል። ለእግዚአብሔር የተሰወረ የለም። ህዝብም ይመለከታል ። በተለይ ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት "ከእግዚአብሔር የተሰጠች ፣ ሃዋርያት የተቀበሏት ፣ አባቶች የጠበቋት ፣ ለእኛም ያስተላለፉልን . . ." እንደሆነች እየነገሩንና እያስተማሩን ዞር ብለው ይህቿን ጣዕሟ እማይጠገብ መሰረቷ ክርስቶስ የሆነችን ቤተ ክርስቲያን አርጅታለችና የማደሱን ሃላፊነት የእኛ ነው ባዮች በቅጥሯንና በምዕመናኗ ላይ ብዙ ፈተናና ችግር ፈጥረዋል።*

*ለቀደሙት ሃዋርያት ፣ ላለፉት ሊቃውተ ቤተ-ክርስቲያን ፣ በኋላም ለተረከቡት አባቶች ያልተገለፀላቸው ፣ ለነርሱ ግን የተገለፀላቸው ነገር ምን ይሆን ያሰኛል? ይህቺ ሃይማኖት የነ ቅዱስ አትናትዮስ ፣ የነቅዱስ ቆርሎስ ፣ እነ ቅዱስ ባስሊዮስ በአለፉት በቀደሙት ሃዋርያት የተመሰረተች ነች ። "አዲስ ሃዋርያ ነኝ . . ." እራሱን ብሎ ፣ ጌታችን መድሃኒታችንን እየሱስ ክርስቶስን "አምላክም ነው አማላጅም ነው . . ." ብሎ ትምህርትን ከየትኞቹ አባቶች ተማሩት ? ያስብላል። ሃዋርያት የምንላቸው ያኔ በጌታ የተመረጡት ፣ የጣመ የላመ ያልበሉ ፣ ሶፋና የመኪና ወንበር ያላዩ ፣ በመንኮራኩር የተፈጩ ፣ ተዘቅዝቀ የተሰቀሉ ናቸው።*

*ጃንደረባው ባኮስ መጽሐፍ ሲያነብ የነበረው በእምነት ነው። ለ1600 አመት ከግብፅ ጋር የነበረው ግንኙነት የእምነት ነው ። 9ኙ ቅዱሳን ቤተ ክርስትያን የተቀበለችው በእምነት ነው ። አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን በዜግነት ኢትዮጵያዊ አልነበሩም። ቅድመ አባቶቻችን ስለዚህ ሁሉ ብቃታቸው በየዋህነትና በእምነት ፅናታቸው ነው። በሃይማኖታዊ ሰው ትልቅም ይሁን ትንሽ ሃጥያት ከሆነ ሃጥያት ነው ። በብዙ ምዕመናን መለኮታዊ እምነት ላይ ዝም ብሎ የራስን ሃሳብ ህዝቡ ሳያወቀው መጫን ከሃጥያትም ሃጥያት ነው። ከታናናሾቹ አንዱን እንኳን ከምታስት የወፍጮ ድንጋይ ከአንገትህ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባህር ብትጣል ይሻልሃል ነው ቃሉ።*

*"ፆሙ ከብዶናል . . ." ከሆነ በግል መተው ይቻላል። የእምነቱ ተከታዮች ግን ያሉት ነገር የለም ። ስለ ቅዳሴ ማጠር መርዘምም የምዕመነን ጥያቄ ሆኖ አያውቅም። ዱላቸውና ወቀሳቸው በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ፣በቅዱሳን አባቶች ፣ በአዋልድ መጽሐፍት ላይ ነው። ኦርቶዶክስ ሃይማኖት በነገረ ድህነት ላይ ከሌሎች የክርስትና እምነት ጋር ያለውን ልዩነት ነውና የነገረ መለኮት ትምህርቷ ተውላት ።*

*በመጽሐፈ ሳሙኤል ላይ ሳኦል ዳዊትን ባስጨነቀው ጊዜ እግዚአብሄር ሳኦልን "ሳኦል . . . ሳኦል ስለምን ታሳድደኛለህ . . ?" አለው። እኛንም በዚህ ዘመን ያለን ያፈነገጥን የቤተ ክርስቲያን ልጆች ይሄንን ጥያቄ እንጠየቃለን። እናንተ ከኔትፍሌክስ( Netflex) ሃሳብ የተዛመዳችሁ እናንት ከሊሲፈር (Lucifer) የተፋቀራችሁ ወንድሞች እህቶች ፣ እናንት የኢሉምናሬን(Luminaries) የጡት ልጅ የሆናችሁ " . . . ለምን ታሳድዱኛላችሁ . . .?" ትላለች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን። እናንተ የልጅ አስጠቂዎች አጥሯን ነቅንቃችሁ አታስነቅንቁ። ለድርጎ ብለን የምናፈርሳት ሳትሆን በመስዋዕነት የምንታደጋት እናት ቤተ ክርስቲያን መሆን አለባት። ተግባባን !*

*የብዙዎቻችን የተሀድሶ አካሄድ መንፈሳዊም ይሁን አገራዊ አደጋውን ያለመረዳትና ክብደት ያለመስጠት አባዜ አለብን። ምን ችግር አለው ባዮች ብዙ ነን፡፡ ሃይማኖቱን በሃይማኖትነቱ ሳይሆን ወገኔ ነው ፣ የሰፈሬ የወንዜ ሰው ነው ብሎ የማሰብ አባዜን ያላብሳል ፣ አላብሷልም። "እነእከሌም ስላሉበት . . ." ብሎ እምነቱን ሳይሆን በጓደኝነት ብቻ በጭፍን ይሄዳል። በመጨረሻ ታድያ በአንድ ሃሳብ ላይ ያለመግባባትን ችግርን ያመጣል።*

*አሁን ብዙ ምዕመናን ሁኔታውን ገብቷቸዋል ፣ ተረድተዋልም ብዬ አስባለሁኝ። እናንተ ልብ ያላችሁ ችግሯ የገባችሁ ፣ የመጥፊያዋ ጉድጓድ እየተማሰለት እንደሆነ የተገለጠላችሁ እንደ ናቡቴ ". . . የአባቶቼን እርስት እሰጥህ (እሰጣችሁ) ዘንድ እግዚዝብሄር ያርቅልኝ . . ." በሉ። (መጽሐፈ ነግስት ቀዳማዊ 21 ፡ 3)። እንደናቡቴም እንሁንላት። ምሳሌ 22፡ 28 "አባቶችህ የሰሩትን የቀድሞውን የድንበር ምልክት አታፍስር" ይላል። ላለ መፍረሷ፣ ላለ መነካቷ እንታትር እንጂ ከአፍራሾቿ ጋር አንተባበር፡፡*

*የተሃድሶ አካሄድ አለምን በአንድ የሃይማኖት ጥላ ስር አሰባስቦ ከአንድ ማዕከል ቦታ እንዳሻው በሃያላን የማሽከርከር የረጅምና ትልም እንቅስቃሴ ትልም ነው። ከዚያ በፊት ግን ዶግማዋን፣ ቀኖናዋን ፣ ትውፊቷንና ባህሏን መበረዝ ነው። ይሄንን ደግሞ የእምነት ጥልቀቱ በሌላቸው በደካማና በተስፋ ቆራጭ ዜጎች ግባቸውን ለማሳካት ይታትራሉ። እነዚህም ነፍሳት ኪሳቸውን ለድርጎ ከፍተው አገርና ህዝብ ሲያሽብሩ ይታያሉ። መጪው ችግር በኋላ እነርሱንም እንድሚጎዳ አይረዱትምና።*

*በተቃራኒው ታድያ ሃይማኖቴንም የቤተ ክርስቲያኗንና ቅጥሯን አናስነካም ያሉትን የዋልድባ መነኮሳትን እንደ አባ ገ/እየሱስ ኪ/ማርያም ፣ እንደ አባ ገብረ ስላሴ ወልደ ሃይማኖት እና ሌሎች ቁርጠኛ ዜጎች የእስር በደል ለአብነት የሚደባባይ ምስክሮች ናቸው። አሳሪዎችን ይጭነቃቸው እንጂ የሃይማኖት አባትማ ግብሩ እንዲህ ነው። መንጋን ይጠብቃል ፣ ቤተ ክርስቲያንን ይታደጋል እንጂ ትቶም አይሸሽም ፣ ይሞትላታል እንጂ አያስገድላትም። በፊተና ውስጥ የመጣችን ሃማኖት አባቶቹ የሰጡትን አደራ እርሱም በመከራዋ ወስጥ አልፎ ለትልዱ ያስረክባል። የሃይማኖት አባት እንዲህ ነው። ". . እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር በእስር ቤት አብሮት ነበር. . ." ነውና በእነዚህ አባቶች ጋርም እግዚአብሔር አብሯቸው ይሆናል። ዮሴፍንም አሳልፈው የተሰጡት ወንድሞቹ ፣ የእኛም አባቶች የተሰጡት በልጆቻቸውና በውንድሞቻቸው ናቸው። የሚገርመው ከላይ በቤተ ክህነት መንበር ላይ ተቀምጦ "መታሰራቸው አግባብ አይደለምና ይፈቱ" ብሎ ማለትም ምን ገደደ? ቢያንስ ልብሱን ያለበሰኳቸው እኔ ነኝና ተውላቸው ለምን አትልም። የምዕመናንስ ዝምታ ለምን?*

ኢትዮጵያና  የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያን የብዙ አመታት ጥልቅ በሆነ የትውልድ መሰረት ላይ የተገቡ በመሆናቸው እንዲህ በቀላሉ የሚፈርሱ አይደሉም። ማንም ግብረገብነት የጎደለው እንዳሻው የሚዳክርባት መሆን የለባትም።  በስንት አባቶችና እናቶች ደምና አጥንት ላይ የተገነባች ነች።  በመላዕክት መንፈስ ቅጥሯን ይጠብቃሉ። እንድሚያስነኳትም እምነት አለን። ክርስቲያና ብረት ደግሞ ይሆንን ይፈልጋል።

ሌላ ደግሞ እንደ ተሃድሶው ሁሉ የቤ/ክርስቲያንዋን መስቀል የያዙ ፣ ከበሮዋን ፣ ጽናጽሏን ፣ መቋሚያዋን ፣ አልባሳቷን ሌሎች ንዋየ ቅድሳቶቿን እየተጠቀሙ ሌላ እምነት አራማጆች "ኤልያስ ከብሄረ ህያዋን ወደ ምድር መጥቷል ፣ የአለም መጨረሻ የኢትዮጵያም ትንሳሄዋ ደርሷል. . ." የሚሉ መስቀል ያንጠለጠሉ የዳዊትን ኮከብ የሰቀሉ "ማህበረ ሰላሴ ደቂቀ ኤልያስ" በሚል ስም ሌላ ቡድኖች ተነስተዋል። የእነዚህንም አካሄድ ከአንዳንድ ሰባኪያንና መምህራን በስተቀር በአባቶች ትኩረት የተሰጠው አይመስልም። የሙብቱ ጉዳይ እንዳለ ሆኖ የቤ/ክርስቲያኗ ንዋየ ቅድሳት የአዕምሮ ንብረት ጥበቃ ወይንም Ownership patent, Copyright) የመሳሰሉትን የህግ ከለላ ተጠቅሞ ለንዋየ ቅድሳትዋ የጥበቃና የከልከላ ማሰሪያ ሊበጅለት ይገባል እላለሁኝ። ነገር ጉልበት አውጥቶ ለመቆጣጠር በሚያስቸግርበት ደረጃ ላይ እስከሚደርስ ደረስና አያሌ የሰው አቅምና ብዙ ገንዘብ እስከሚያስወጣ ድረስ መጠበቅ የለበትም። ማህበረ ቅዱሳን ባይኖሩ ኖሮ የተሃድሶውን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ከዚህ በላይ ባስቸገረ ነበረ። አሁንም ተከታታይ ስራ ግን የሚሻው ይመስላል።

## አገራዊ ጉዳይ

ይህንን ጉዳይ በአንድ እጃችን ይዘን ወደ አገራዊ ጉዳይ ስንመለሰው መልኩ ባህሪውና ተግዳሮቱ ሌላ ቁመና ያሳየናል። የዋህ ምዕመናንን ከፊት ያስቀድሙና ለነገ መደላደላቸው ፣ ለአለማዊ ፍስሃቸው ኢትዮጵያዊ እሴትንና ባህልን የማጥፋት ደባቸው በረጃጅም እጆቻቸው መታሰራችንንና መታመሳችንን እንመለከታለን። የሚገርመው ተጽፎልንም ፣ ተነግሮንም ያለመስማታችን ጉዳይ ነው።

ከትናንቱ ወድቀታችን ዛሬ አለመማራችን ሌላው መሰናከላችን ነው። "ያልጠፋነው በእግዚአብሔር ቸርነት ነው . . ." እንዳለው ነው እንጂ ጦርነቱ የበረታ ፣ የችግሩ ጫፍ የረዘመ ፣ የተንኮል ጉንጉን የረቀቀ እንደሆነ የሚነግሩን ሚስጢሩን የሚያቁ አባትና እናቶች ብዙ ናቸው ። " የጋራ ነው . ." በምንልበት ጉዳይ ላይ አንድና ሁለት ሰው ብቻ የፈለገቱን ሲወስኑና ያሻቸውን ሲያደርጉ አብዝሃውን ሲበትኑና አዘቅጥ ወስጥ ሲከቱ ፣ መከራን ሲያፀኑበት ይስተውላል። ይህ በተለይ በስደቱ አለም የከፋ ነው።

በክርስትናና በእስልምና አስተምሮት ላይ የተለየ ሃሳብና ባህሪይ በማምጣት በአገራዊ ፣ በህዝባዊ በኢኮኖሚያዊ በፖለቲካዊ ይዘትና ጉዳይ ላይ ዜጎች ያለንን ፀባይ የማሰቀየር ዘመቻ ነው። በአሁኑ መንግስት እየታየና ከመቼውም ጊዜ በላይ የላቀ አደገኛ ጉዳይ ሆዋል። በአደባባይ ወጥቶ " . . . የኦርቶዶክስ እምነትና አማራውን ቀብረነዋል። . . ." ብሎ በአዛውንት ቦተሊከኞች ሲነገር ማድመጥና በአገራዊ ስሜት ወስጥ ሆኖ መስማት ያሰቀጥጣል። ኢትዮጵያዊ ከሆነ ሰው ፣ ኢትዮጵያዊ ከሆነ ፖለቲከኛ ነኝ ባይ ሰው እንዲህ አይነት ነገር መስማት የዝቅጠት ልኩ ገደቡን ማለፉን ያሳያል። አንድን አገር ለመምራት መጀመሪያ ግብረገብነት ያስፈልጋል ፣ ሌላውና ትልቁ ቁምነገር የአገሪቱን ታሪካዊ  ጠላቶቿንና ወዳጅና በደንብ መለየት ያስፈልጋል። የትምህርት ዝግጅት እንዳለ ሆኖ፡፡ ይህ ባልሆነበት እዕምሮ በጥላቻ መንፈስ ተገንዞ አገር መምራት አይቻልም።

በአንድ እምነት ወስጥ ያሉ መምህራን አገርንና እምነትን ፣ እምነትንና አገርን ፍጹም ለያይተው የሚያስተምሩህ ከሆነ ሊነጥቁህ የፈለጉት ነገር አለ ማለት ነው። እግዚአብሄር ለእስራኤላውያንን ከንአንን ሲያወርሳቸው ያቺን ምድር መርጦላቸዋል ። ስለዚህ እስራኤላዊ ሁሉ ለዚያች ምድር ቢሞት ቢዋጋ

እውነትነት አላቸው። እምነታቸውን ከአገራቸው ጋር በፅኑ የሚገናኙ መሆናቸውን ያውቃሉ። እምነት ያለአገር አይሆንም ፣ አገር ደግሞ በህዝብና በእምነት ትፀናለች። እኛም ኢትዮጵያውያን ሁኔታው ከዚህ በላይ ይሆን እንደሆን እንጂ ያነሰ አገራዊና ሃይማኖታዊ ስሜት ሊኖረን አይገባም። አገርንና ሃይማኖትን የነጣጠለ ኦርቶዶክሳዊ ስሜትና ትምህርት ካለ ፤ ተማሪው ያስተውል።

ክረምት “ክት. . ክት” ብሎ የሳቀባቸውን ወይንም የሚስቅባቸውን ህፀዋቶች መሆን የለብንም። የወይን እፅና በአንዳንድ በምዕራቡ አለም በተለይ ከምድር ወገብ ርቀው የሚበቅሉ እፅዋቶች የዝናብ ወቅት ሲመጣ ምድር በዝናብ ስትርስ ሌሎች አትክልቶች ሲያጎነቅሉ ተራሮች በልምላሜ ሲዋጡ እነርሱ ግን ቅጠሎቻቸውን አርግፈው ቅርጫፎቻቸውን አንጨፍረው ክረምቱን ሙሉ ዘለላ ቅጠል ሳይጥልባቸው ያልፋሉ። ቀድሞ በነበረው በጋ ግን እነርሱን የመሰለ ለም እንጨት አልነበረም። በበጋ ውስጥ ሆኖ መቼም ቢሆን እንዲህ ይሆናሉ ብሎ የሚል አልነበረም። ውስጡን ለማያውቅና በክረምት ይህንን እንጨት ያየ “ምነው ይሄንን የደረቀ ጭራሮ ቆርጠው ቢጥሉት” ያሰኛል።

እኛም ኢትዮጵያውያን እንደዚህ መሆን የለብንም። አገራችን በክረምት ውስጥ ነበረች። ከመሪ በቀር ሁሉ አላት። የእምነት ክረምት ናት፣ የህብረተሰብ የመቻቻል ክረምት ናት ፣ የተፈጥሯዊ ሃብት ክረምት ናት፣ የቆየ የደለበ ባለታሪክ እመቤት ናት። በገዛ እጃችን ያስነጠቅነውን አስነጥቀን ፣ ያስወሰድነውን አስወስደን ከእዚህ ደርሰናል። አሁንም ብዙ አለን ። አገር ግርግር ላይ ነች ። ግርግር ድግሞ ለሌባ ይመቻል። አለም ነጣቂ ነች። የተኩላ ባህሪ አላት። አሁንም በዚህ ግርግር ያለንን ተፈጥሯዊና ቁሳዊ እሴቶቻችንን አስነጥቀን ጭራሮዎቻችን ብቻ አጨፍረን ፣ ለምለም ባህሪያችንን አጥተን ክረምት የሳቀባቸው ህፀዋቶች እንዳንሆን አደራ። ክት-ክት ብሎ አለም እንዳይስቅብን። ገዳማትን የሚያፈርስን ፣ አባቶችን የሚያስግዝን ፣ የውርቅ መሬታችንን የሚያሸጠን ፣ በሬና ላሞቻንን አስልፎ ያስጠን ፣ አህያን ያሳረደን ፣ ህፃናትን የምንገድል ፣ እናቶችንን የምናስለቅስ ሰይጣናዊ ባህሪ ተጠናውቶናል። ብዙዎችንን ንዋይ ከመጠን በላይ ማንነታችንና እምነታችንን እየቀማን ነው። ወደልቦናችን እንመለስ።

## ኢትዮጵያዊ ፀባያችን

ጥንት ድሮ የነበረ የደረጀ ኢትዮጵያዊ ፀባያችን ከዘመን ጋር ተሸርሽሮ እየተቀየረ ነው ለማለት የምንደፍርበት ደረጃ ላይ የደረስን ይመስላል። ሃይማኖታዊ ፀባያችን ፣ አገራዊ ፀባያችን ፣ ወገናዊና አትኩኝ ባይነት ፀባያችን የተቀየረው መሰለ። የዚህ ሁሉ የባህሪ ለውጥ የእኛ የሆኑትን ነገሮች ሌሎች እንዲነኩብን ስለምንፈቅድና ስለምናስነካም ጭምር ነው። በአገር ጉዳይ ላይ መደራደሩ የመጣውአሁን ነው። “የአገሬን አፈር በእግሩ ይዞ እንዳይሄድ ፣ እግሩን አጥባችሁ ሸኙልኝ:. . .” ያሉ አባቶች ነበሩን። ድንበር ቆርሰው የሚሸጡ ፣ የባህር በር ለአንድ አገር እንደተራ ሸቀጥ ነው የሚሉንን ድኩማን መሪዎችን በወንበር ላይ አሹመን ተቀብለን እየኖርን ነው። በባዕዳን የተነገረንን ነገሮች በጥርጣሬ ከማየት ይልቅ እንደወረደ እንደተነገረን እውነት ብለን ተቀባይ መሆናችን ነው። “ . . . ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዝንጉርጉርነቱን ይቀይራልን . . .? ” የተባለውን በገዛ እጃችን ከመጽሃፍ ልንፍቀው የተዘጋጅን ይመስላል።

አሁን አሁንማ ኢትዮጵያዊ ፀባያችን ሃይማኖታችንን እንደማያውቅ ፣ ህዝባችንን እንደማያውቅ ፣ አንድነታችን ህብረታችን መሆኑን እንደማያውቅ ሆንን። የአባቶቻችንን ራዕይ የረሳን ፣ አገራዊ መስመራችንን የሳትን መሰለ። የተቀረነው በየእራሳችን ትንንሽ ማሰሮዎቻችን ወስጥ ለብቻችን መንተክተክ ልማድ አደረግነው። ህዝብ በአንድ ሃሳብ ላይ መተባበር በምንሊክ በአድዋ ጦርንርት ጊዜ ወጤቱን አይተን ነበረ ግን አልተማርንበትም። የቀዬ ሰው ፣ መንፈሰ-መንደርተኛ ሆንን።

የአባቶቻችንን ፀሎታቸውን መፀለይ ከበደን ፣ አፅዋማታቸውን መፆም ሲጋዊ ባህሪያችን አሸነፈን ፣ ቅዳሴያቸው ረዘመብን አልን። ለአገራችንና ለእኛነታችን የምንሰጠው ዋጋ ከሚገባው በታች ጎትተን አውረድነው። ራህይ ዮሃንስ 2፡ 25 "እስከምመጣ ያላችሁን ጠብቁ" ያለውን ዘነጋነው። የተባልነውን ለመጠበቅ ያለንን ነገር ለማወቅም ከበደን ። የተሰጠንን ንቀን አስናቅነው። ችግሩ የተሰጠን እምነት ታላቅ መሆኑ ቀድመውን አውቀው እነርሱ ስላላገኙትና ስላልታደሉት ነቀፌታ የመሰለችውን አጉልተው አሳዩንና እንደበቀቀን ያንን ይዘን ማስተጋንባት ስራችን አደረግነው። ቆም ብሎ መመርመር አዋቂዎችን መጠየቅ ነውር መሰለ። ይሄ ደግሞ በቦታው ላይ ያለው ሰው የእውቀት ዝግጅት ደካማ በሆኑ የመጣ ጣጣ ነው። ቢያንስ ያፍርሱን እንጂ በማፈረሱ አንተባበር፡፡ " . . .ያአባትህ ቤት ሲዘረፍ አንተም አብረህ ዝረፍ . . . ." አጉል ተረት ነውና እንተወው። ሮሜ 14:16 ለአንተ ያለው መልካም ነገር አይሰደብ ፡ ይላል። የተሰጠንን ፀጋና በረከት ባናሰደበው መልካም ነው።

በዚህ በውያኔ ዘመን ያሰደብነው ብዙ ነገር አለ። ሃይማኖታችንን አሰደብን ፣ ኢድዋን ገድሉንና ምንሊክን አሰደብን ፣ "ብሄር ብሄረሰቦች . . ." እያልን ከፍና ዝቅ እየተደራረግን ተሰዳደብን ፣ ትንንሽን ጎጇችንን አፍቅረን ኢትዮጵያዊ ድንኳናችንን  አሰደብነው። እግዚአብሄር ያከበረንን ክብር የሰጠንን ፀጋና በረከት መጠበቅ ካቃተን መልሶ እንደ ጠቢቡ ሰለሞን መነጠቅ አለ። "በተቀደሰ ስፍራ ላይ እርኩስ መንፈስን . . ." ከማቆም እንጠንቀቅ። የድሮው የቀደመው ኢትዮጵያዊ መልካችን መልካም ነውና አንቀይር ። ተስፋችን በእግዚአብሄር ነው ትውልዱም አያሳፍርም።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከአገር እስከ አህጉረ አፍሪካ ፣ ለአለምም ጭምር ውለታዋ ብዙ ነበር። ፊደል ቀርፃ ብራና ፍቃ ቀለም በጥብጣ አለማዊም ይሁን መለኮታዊ ብርሃንን ፈንጥቃለች። ጦር መጣ ቢሏት ምዕመናኗን በውዴታም በግዝትም አዋግታለች ተዋግታለች። የቀደመ የደቡብ አፍሪካ መሪ ታቦ ምቤኪ ለክብር ሽልማት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተገኝተው ያደረጉት ንግግር "የኢትዮጵያ ቤ/ክርስቲያን አፍሪካን ነፃ በማውጣትና በነፃነት ጎዳናም እንድንሄድ ትልቅ አስተዋጾ አበርክታለች" ብሏል። (July 24 2010 Adiss Ababa University Speech).

በ1830 ዓ.ም. Sir Francis Bond head የተባለ አውሮፓዊ ሰለኢትዮጵያ ክርስትና ሲጽፍ እንዲህ ብሎ ነበር። "የክርስትና ሃይማኖት ዘሯ በአብሲንያ ተራሮች ላይ እንዳገኘችው ያለ አፈር ለቡቃያዋ ተስማሚ የሆነ መሬት ሌላ ቦታ አግኝታ አታውቅም።" ብሎ ነበር። ሌሎችም ብዙ ብለውላታል ።

በመጨረሻ ይሄንን የመሰለ አሳብ ሲነሳ ነፍሳቸውን ይማርና የአባታችንን የብጹዕ አቡነ ሰላማ ሊቀ ጳጳስ የ1992 ዓ.ም. ከልብ  ከማይጠፋ ስብከታቸው ጠቅሶ መለፍ አግባብ ነውና እንዲህ ብለው ነበር " . . የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክርስቲያንን በገንዘብ ተመክተው ሊያንገላቷት ተነስተዋል። አምላኳ ግን አያንገላታትም ፣ አገራችንም(ኢትዮጵያ) እንዲህ በመዋዛ የምትፈረከስ እራስ አይደለችም . ."ብለው ነበር ።

ለልብ ብርታት ፣ ለድካም ጽናት የሚሆኑ እንዲህ አይነት አባቶች ትምህርታቸውንና መንፈሳቸውን ይዘን ዘመን እንሻገራለን ፡፡ አለም ችግር አስታቅፋን ትልቅነታችንን እንዳትወስደው እንጠንቀቅ፡፡ ወርቆቻችንን በጠጠር ፣ ፍቅራችንን በንትርክ አንዳንቀይር። "ስዶ ማሳደደ ካማረህ ዶሮህን በቆቅ ቀይር" አበው ይላሉና። ብርታትና ጥንካሬ ይሆነን ዘንድ እግዚአብሔር አብሮን ይሁን፡፡ እኛም መልካችንን አንቀይረው !

ቀለም ተበጥብጦ ብራና ተፍቆ ፣ በገፅ ከኖረው
ገላህ ላይ በወጣ ፣ ከልብ በፃፈው
በተነገረልህ በተመሰከረ ፣ በእምነት ቃል በዋ
የአይንህን ድፍረት የግንባርህን ኩራት ፣ አብሮህ በበቀለ
በውስጥህ ደርጅቶ ፣ በውስጥህ በኖረው . . .
አደራ ልበልህ . . . አደራ ልንገርህ ፣ ዥንጉርጉር መልክህን እንዳትቀይረው

እንዳትቀይረው . . .  እንዳትለውጠው
ተፈጥሮ ለግሶ ፣ ልዩ የሚያደርግህ
ባልተዋስከው ፀባይ ባልተዋስከው አካል ፣ አንተን የሚያስጌጥህ

በልዕልና ጫፍ ላይ ከፍ አ'ርጎ እምያቆይህ ፣ ዉበትህ እርሱ ነው
አደራ ነውና አደራ ልበልህ ፣ ዥንጉርጉር መልክህን እንዳትቀይረው ።

ፍሬዘውድ ተስፋዬ
ሜልበርን
መጋቢት 2010
antachew@hotmail.com